# ዜና፡ዕረፍት፤

ሊቀ፡ምሁር፡ለይኩን፡ብርሃኑ፣



ከጥር፡፲፱፻፴፯፡ዓመተ፡ምሕረት፡
እስከ፡ግንቦት፡፳፻፩፡ዓመተ፡ምሕረት፤

ኀዘናችን፡በዛ፡መማጸናችን፣
ደጋጎችን፡አጥተን፡ምሁሮቻችንን።
ለይኩን፡ብርሃኑ፡እያልን፡ስንማለል፣
ጭራሹ፡ጨልሞብን፡ተደናግጠናል፣
በድንገት፡ሲለዩን፡ደግ፡ሰው፡አያል።
የእኛ፡ኃጢአት፡ይሁን፡ወይስ፡ያምላክ፡ቁጣ፣
አገር፡ወዳዶችን፡በተራ፡ስናጣ።
ተነሥ፡ብለው፡ጽፈው፡እያስነበቡን፣
ለምን፡ታንገለጉ፡ብለው፡ጠይቀውን፤
በሃይማኖት፡ካባ፡የሚሠራ፡ደባ፣
በማለት፡መክረውን፡እኛ፡እንድንግባባ፤
ፀፀት፡ያሉትንም፡ይኸው፡ተፀፀትን፣
ደጉ፡መምህራችን፡እርስዎን፡አጥተን።
ልሣነ፡ግዕዝን፡ተማሩ፡ሲሉን፣
ባልተለዩን፡እንጂ፡ይዘናል፡ጥናቱን፣
ስላዘጋጁልን፡መዝገበ፡ቃላቱን።
ተክለ፡ሃይማኖት፡ንጉሠ፡ጐጃም፡ወከፋ፣
በሚል፡ርዕስ፡የጻፉትም፡ባልከፋ፤
ግን፣ተጻጽፈን፡ነበር፡አስታውሳለሁኝ፣
በሁለት፡ወራት፡ውስጥ፡ይወጣል፡ብለውኝ፤
ምነው፡ቸኮሉ፡ለጉዞዎ፣
ታትሞ፡ሳይወጣ፡ማረግዎ።
ሕዋ፡ስሌዳውም፡ያስተዋወቀንን፣
ዐራት፣አምስት፡ዓመት፡ሐሣብ፡ተለዋውጠን፣
ተደስተን፡ኖረን፡የዛሬው፡መርዶ፡ችን፣
ከብዶናል፡ይወቁት፡ጥልቅ፡ነው፡ፍቅራችን፣
በእርስዎ፡ላይ፡ያለን፡ሐሣብ፡ምኞታችን፣
ውጥን፡ሳይጨርሱ፡በመለየታችን፣
የእሩቅ፡ዕቅድዎን፣ያገር፡መውደድዎን፣
ሕዝብ፡ሊያውቅ፡ይገባል፡አደካከምዎን።
ሥራ፡ምስክሩ፡ኢትዮጵያዊነቱ፣
ሀገሩ፡ሆነና፡ሃይማኖት፡እምነቱ፣
ሳይቀድሙኝ፡ልቅደም፡ሲል፡ተለየን፡በጧቱ፣
ለሰማዕት፡ለይኩን፡ክቡር፡ሞቱ።
ለይኩን፡ብርሃኑ፡ርኅሩኅ፡ሰው፣
ሊቀ፡ምሁራችን፡ቀን፡ተሌት፡ጣሪው፣
እግዜር፡ይባርክዎ፡ነፍስዎን፡ይማረው።
ለዘመድ፡አዝማዶቻቸው፡እና፡ለቤት፡
ሰወቻቸውም፡እግዚአብሔር፡ያጥናችሁ፡
እላለሁ።
አክባሪያቸው፣
ስለሺ፡ነህ፡ገላነህ፣
ካናዳ።

sileshineh@yahoo.com
ግንቦት፡፳፮፡ቀን፡፳፻፩፡ዓመተ፡ምሕረት፤